# " ደም ተቀብቶ ዝንብ አይፈሩም ! "

# ለኤፍሬም ማዴቦ ከ«አዞ ደርሶ መልስ» አጸፋ፣

ተክሌ የሻው

ከመነሻው የኤፍሬም ማዴቦ ጽሑፍ በእርሱና በግንቦት 7 መካከል ያመለካከትና ያካሄድ ልዩነት እንደአለ ጽሑፉ ፍንጭ ይሰጣል። ሲጀምር በግንቦት 7 አመራር አባልነቱ፣ ለግንቦት 7 ድጋፍ ለማሰባሰብ ኦሽኒያ እና ኒውዝላንድ ድረስ ተጉዞ፣ በጉዞው ያየውንና የታዘበውን በድርጅቱ ስም ከመጻፍ ተቆጥቦ፣ በጽሑፉ ውስጥ የሰፈሩት ሀሳቦች «የእሱና የእሱ ብቻ» እንደሆነ እንዲያዝለት ይማጸናል። «እሣት ካየው ምን ለየው» ይሏል ይህ ነው።

ግንቦት 7 ማለት አመራሮቹና አባሎቹ ናቸው። አባሎቹ ያሉት፣ የተናገሩት ደግሞ፣ እንዳው አልን ለማለት፣ የዋሆችን ለማታለል ካልተፈለገ በቀር «አቅማዳ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ አቅማዳ» ከመሆን የሚለውጠው አንዳችም ነገር የለም። አባባሉ የኔ ብቻ ነው የሚለው፣ በርሱና በድርጅቱ መካከል ልዩነት መኖሩን ወይም ልዩነት ሊፈጥር ይችላል ከሚል እሳቤ የተነሳ እንደሆን ጠቋሚ ነው። ወይም በሰፈረው ሀሳብ በድርጅቱ ውስጥ ጥያቄ ቢያስነሳ፣ ማስነሳቱም አይቀሬ ነው፣ የግሌ ነው ያልኩት እኮ ከዚህ ተጠያቂነት ለማምለጥ ነው ለማለት የተሰላ ስሌት ይመስላል።

ለልዩነቱ መሠረት የሚሆነውም፣ ድርጅቱ ላለፉት 9 ዓመታት «አደርገዋለሁ፣ እሠራዋለሁ» እያለ ቃል እየገባ ከሕዝቡ ገንዘብ እየሰበሰበ በዘጠኝ ዓመት ውስጥ ለገንዘብ ከፋዩ ሕዝብ በዓይን የሚታይ፣ በእጅ የሚጨበጥ ውጤት ማሳየት አለመቻሉ አንዱ ነው። ግንቦት 7 ትልቅ ሥራ ሠርቷል የሚያሰኘው ኢሣትን (የኢትዮጵያ ሣተላይት ቴሌቪዥንና ራዲዮ)ማቋቋሙ ነበር። በዚህም የግንቦት 7 ሊቀመንበር የዜና አውታሩን በማቋቋሙ እንደሚመካ ባንድ ወቅት ለሕዝብ መናገሩ ይታወቃል። ግንቦት 7 መመካት ካለበትም ዕውነተኛ የሥራው ውጤት በሆነው በኢሣት ቢመካ የተገባ በሆነ ነበር። ይህን ግን ሁለቱ የተቋሙ ሥራ አመራር ኃላፊዎች የሆኑት አቶ ታማኝ በየነና አቶ አበበ ገላው«ግመል ሰርቆ አጎንብሶ» የሚሉት ነገር ፣ «የለም ኢሣት ነፃ ሜዲያ ነው፤ የግንቦት 7 እጅም ፣ባለቤትነትም የለበትም» ሲሉ፣ ጠያቂም ኢሣት፣ ተጠያቂም ኢሣት በሆነበት ዝግጅት ሲናገሩ ተሰምተዋል። ይህም ግንቦት 7 ሠራው ተብሎ በኅብረተሰቡ ሞገስ ያገኘለትን ተግባር የእርሱ እንዳልሆነ በራሱ ሰዎች ሲነገር ስንሰማ፣ አግ 7 የአየር ባየር ፖለቲካ የሚያካሂድ እንደሆነ እየሰማን ነው። ከሁሉም በላይ የሐምሌ 5 ቀን 2008 ዓም በኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ የተተኮሰች ጥይት፣ «ጎንደርና አዘዞ ላይ ፊሽካው ተነፋ» ተብሎ የታወጀው የጦርነት አዋጅ፣ ከዓመት በኋላ ዕውነተኛው ጥይት በጀግኖቹ የጎንደር ልጆች ሲተኮስ እና ግንቦት 7 «ድረሱልን፣ ሠራዊት ከሌላችሁ ጥይትና መሣሪያ አቀብሉን» የሚል የሕዝብ ድምፅ ሲሰማ፣ የኤፍሬም ማዴቦው ግንቦት 7 የውኃ ሽታ መሆኑ ሌላው ግንቦት 7 በአየር ላይ እንጂ፣ በመሬት የሌለ መሆኑን ያጋለጠ ተግባር ሆነ።

ጎንደር፣ ጎጃምና ሸዋ በተቀጣጠለው የዐማራ ሕዝብ የማንነትና የኅልውና ሕዝባዊ እንቢተኝነት እንቅስቃሴ፣ከሻዕቢያና ከኢሳያስ አፈወርቂ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መረጋገጥና ለዐማራው ኅልውና መጠበቅ የሚበጅ ነገር ይገኛል ማለት፣«ከእባብ ዕንቅላል፣ እርግብ መጠበቅ ነው» ብለው የሚያምኑ ወገኖች ሳይቀር፣ «እስኪ እንያቸው፣ ጊዜ እንስጣቸው» በማለት ድጋፋቸውን አንዳንዱ በገፍ፣ ሌላው በመቅኑን ይለግሳቸው የነበረው፣ በዕውነተኛ ጦር ሜዳ የሚሰለፍ ሠራዊት ቀርቶ ጥይትና መሳሪያ የሚያቀብል ሰው አለመገኘት፣ ለካ እንደሚባለው «ግንቦት 7 የቁጩ ነው፣ ድሮስ ከሻዕቢያና ከኢሳያስ ለኢትዮጵያ የሚበጅ መጠበቃችን ስሕተት ነው» የሚለው አመለካከት መሬት የያዘ ሆኖ ወጣ።

ኢትዮጵያ እንድትበታተን 30 ዓመታት በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ሲታገዝ ከነበረ ድርጅትና ይህኑ ዓላማውን ካሳካ ድርጅትና አመራር፣ ኢትዮጵያን የሚያድን መድኃኒት ይገኛል ማለት የአስተሳሰብ ችግር ብቻ ሳይሆን፣ ወዳጅና ጠላትን በቅጡ አለማወቅ ነው። ለነገሩ ይህ አባባል ዕውነት የሚሆነው ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ለሚያምን ድርጅትና ግለሰብ ነው። ለወያኔና ለሸዕቢያ ለሚሠሩ ሰዎችና ድርጅቶች፣ ዐማራው ጠላታችን ነው፣ ኢትዮጵያዊነትን በኃይል የጫተነብን ነው ብለው

ለሚያምኑ ቡድኖችና ግለሰቦች ሻዕቢያ ወዳጅ ነው። ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን እታደጋለሁ የሚሉ ቡድኖች በምንም ተዓምር ከሻዕቢያ ጉያ አይገቡም። ሻዕቢያ የዐማራና የኢትዮጵያዊነት ዐውራ ጠላት ነውና። ወዳጅና ጠላቱን ያልለየ ድርጅትና አመራር ደግሞ እንኳን ለአገርና ለሕዝብ ቤዛ ሊሆን፣ ለራሱም ኅልውና ዋስትና የለውም። ከሁሉም በላይ በታሪኩ፣ በቁጥሩ፣ በኢትዮጵያዊነት እምነቱ ከፍተኛ የሆነውን የዐማራውን ነገድ በጠላትነት ፈርጆ ስለኢትዮጵያ አንድነት መስበክ «ሆድ ሲያውቅ፣ ዶሮ ማታ» መሆኑን ዘግይተውም ቢሆን የተገነዘቡ ሰዎች ለግንቦት 7 ጀርባርቸውን መስጠት መጀመራቸው ያስፈራው ኤፍሬም፣ ሀሳቡን እንደልቡና እንደተሰማው፣ ራሱን ከድርጅት ማዕቀፍ ውስጥ አውጥቶ ለመዋኘት መፈለጉ ሀሳቡ የእኔና የእኔ ብቻ ነው ሲል ተማፀነ። ይህ ስልቱ ግን ልዩነቱን ከማጉላት ውጭ ያጠበዋል ተብሎ አይታሰብም። ኤፍሬም የተለመደውን ገንዘብ «በኬሻ» ይዤ እመለሳለሁ ብሎ ያን ሁሉ አስፈሪ ያለውን ጉዞ ተጉዞ፣ ባዶ እጁን ለመመለሱ ምክንያቱ እሱና ድርጅቱ የተከተሉት ዓላማ ስሕተት መሆኑን ማመን ተስኖት፣ ድርጅቱ የጠበቀውን የተለመደ ገንዘብ ሳይዝ የመመለሱ ምክንያት ዐማራው ለኅልውናውና በማምነቱ ዙሪያ ለመሰባሰብ እያደረገ ያለውን ትግል፣ በአስከፊነትና በአስፈሪነት መልኩ ሊስለው ሞክሯል።
የዐማራንም መደራጀት ከኦሮሞ፣ ከኦጋዴን፣ ከሲዳማ፣ ከአፋር፣ከትግሬ፣ከኤርትራ ወዘተ ነፃ አውጭ ድርጅቶች በላይ አስፈርቶታል። ለነዚህ መደራጀት ዕውቅና ሰጥቶ፣ የዐማራውን በዐማራነቱ መደራጀትን ይኮንናል።

የኩነኔው መሠረቱም ዐማራው በማንነቱ መደራጀት ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ከሚል ቀና እሳቤ የሚመነጭ አይደለም። የዐማራው መደራጀት ለነባሯ ኢትዮጵያ አንድነት ትንሣኤ እንደሚሆን ግንቦት 7 እና ኤፍሬም ማዴቦ በሚገባ ይገባቸዋል። ይሁን እንጂ፣የዐማራው መደራጀት የጌታቸውን የሻዕቢያ ፍላጎት በእጅጉ ይፃረርባቸዋል። ይህ መፃረር ደግሞ አግ 7 በዐማራው ሁለንተናዊ ኪሣራ ፣በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም እና ግዛታዊ አንድነት ላይ ተረማምዶ የተሸራረፈች፣ ወያኔ የሳላት ኢትዮጵያ ገዥ ለመሆን ያላቸውን ዕቅድ ያከሽፋል። ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ባለቤትነቷን ተነጥቃ እንድትቀር ግንቦት 7 እና ኤፍሬም ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ጽኑ ዕምነት አላቸው። ይህ ዕምነት ባይኖራቸው፣ በምንም ተዓምር ከወያኔ ጋር ለሚደረግ ትግል ኤርትራን ምሽግና መረማመጃ ማድረግ ሳይሆን፣ ሊያስቡት አይቻላቸውም ነበር። ቀይባሕር የኢትዮጵያ ተፈጥሮአዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ በር መሆኑን ግንቦቴዎች አይቀበሉም። የቀረው ቢቀር አሰብ የኢትዮጵያ እንደሆነና መሆንም እንዳለበት አይቀበሉም። በዚህ ዕምነታቸው መሠረትም ነው ኤርትራ የመሸጉት።
ሌላው የኩነኔ ምክንያት የምኒልክ ዘር ወደ ፖለቲካ መድረክ እንዳይወጣ ካለው ጭፍን የዘር ጥላቻ ነው። ኤፍሬምና ግንቦት 7 ዐማራውን የሚፈልጉት ለገንዘቡ፣ ለጦር ማገዶነቱ፣ ለማስተናገዱ፣ ለወንበር ደርዳሪነቱ እና ለአጃቢነቱ ነው። ከዚህ አልፎ እኔም ሰው ነኝና የሰውነት መብትና ክብሬ ይጠበቅ የሚል ጥያቄ ሲያነሳ፣ በጭራቅነት ይመስሉታል።

በጥቅሉ ስለኤፍሬም ማዴቦ እርስ በርሱ የሚጣፋ የዜሮ ድምር የቃላት ክምር ጽሑፍ ይህን ካልኩ፣ በጽሑፉ ያነሳቸውን መሠረታዊ ናቸው ባላቸው ጉዳዮች ላይ የእኔን ዕይታ አንድ ባንድ ለማሳየት ልሞክር።

1 «አደራ ቦቅቧቃ እንዳትሉኝ!(phobia) እንጂ፣ ፍርሀት የለኝም።» ይላል። «ምን ያለበት ዝላይ አይችልም» ይባላል። ካልፈራ ፍርሀትን ምን አስነሳው። መፍራት የሰው ልጆች ባሕሪ ነው። ጀግነነት ከፍርሀት፣ (ላለመሞት፣ ላለመቀደም፣ዓላማን ላለመነጠቅ) ከሚመነጭ ፍርሐት የሚወለድ ነው። ይህን ሳይገነዘብ፣ፍርሐቱን በተውሶ ቋንቋ ፎቢያ ይለናል። በራስ አለመተማመን፣ ራስን ፣ ተፈጥሮን አለመሆን አንዱ ማሳያ ነው። ይህ አባባል፣ ፎቢያም እንበለው ፍርሐት፣ «እሳት ካየው ምን ለየው» ዓይነት ነው። ልቡ እና እምነቱ የፈራ መሆኑን እየነገረን፣«ሰው ፈርቶ ወደ ሞት አይሄድም» ይለናል። በእርሱ ቤት አሥመራ መቀመጡ ሞት መሆኑ ነው። እኔ ደግሞ አሥመራ የሄደው ገድሎ ለመሞት እንጂ፣ አስቀድሞ ሞቶ ለመጠበቅ አልመሰለኝም ነበር። ሞት ደግሞ ካሉበት ቦታ፣የትም ቦታ ይገድላል እንጂ፣ መግደያ የተለየ ቦታ የለውም። ጦርነት ሲሄድ ሊገድል ፣ በድል ሊመለስ የኅሊና ዝግጅት አድርጎ እንጂ፣ እሞታለሁ ብሎ ካለ መሄድ አያሻውም። የጦር ሰው የተተኮሰ ጥይት ሁሉ ሰው አይገድልም ብሎ የሚያምን ነው። አዋጊዎቹ «ጥይት ጉድጓዷን ታውቃለች» ብለው ነው የሚያምኑት፣ ሠራዊታቸውምን የሚያበረታቱት፣አትሞትም፣ የተተኮሰ ጥይት ሁሉ ሰው አይገድልም፤ ነገ ባለታሪክ ጀግና ትሆናለህ ብለው እንጂ፣ የምትሄደው ለሞት ነው ብለው አይደለም። ይህ ከሆነማ ድል የለም። ለዚህም ይመስላል ግንቦት 7 ጥይት የሚተኩስ ሰው ያጣው። መሪዎቹ መርተው ለድል የሚያበቁ ሳይሆኑ፣ አስቀድመው ሞትን የሚያስታውሱ መሆናቸውን፣ገድለው በድል ለመመለስ ያልቆረጡ መሆኑን፣ ተከታይ ማፍራት ያላስቻላቸው እንደሆን ኤፍሬም በተዘዋዋሪ እየነገር ነው። ሞት ካሉበት ድረስ ይመጣል እንጂ፣ መሄድን አይጠይቅም። አይዞን ኤፍሬም! ሞት አሥመራም ሆንክ፣ ቨርጂኒያ፣ አውሮፓም ሆንክ አፍሪካ ቅጥብ ቀንህ ስትደርስ የማትቀርባት የተፈጥሮ ዕውደት ነው። እናም ለተከታዮችህ ሞትን ሳይሆን፣ መግደልን፣ ፍርሐትን ሳይሆን፣ ጀግንነትን አስተምራቸው። ከዛሬ ባሻገር ስለሚኖረው መልካም ነገር ንገራቸው! አመራር በአርአያነት

ነውና!
ኤፍሬም በዕውነት ከላይ ፎቢያ እንጂ፣ ፍርሐት የለብኝም ያለውን፣ ዝቅ ይልና፣ «የአውሮፕላን ጉዞና ፍርሐቱ ግን፣ ሸገር ገብቸ እፎይ እስክል ድረስ ይቀጥላል» ይለናል። ይህ አባባል ፍርሐቱን ከመግለጹም በላይ፣ የላይኛውን ያጣፋል። በሌላ በኩል፣ የኢትዮጵያና የአፍሪካ መዲና የሆነችውን አዲስ አበባን፣ አዲስ አበባ ብሎ ለመጥራት አለመፈለጉን ያሳያል። ያለመፈለጉ መሠረታዊ ምክንያትም የኦነግ ዓላማ አራማጅ፣ ኦሮሚያ የምትባል አገር ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ እንዲመሠረት ጽኑ እምነቱ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል። ይህም ኢትዮጵያ በዘመን ፍሰት፣ በተፈጥሮ ገፊና ሳቢ ኃይሎች፣ በንግድ፣ በጦርነት፣ በፍልሰት፣ በጋብቻ ወዘተ አማካኝነት በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ነገድና ጎሳዎች ተቀላቅለው፣ ተዋሕደው፣ አንድ ኢትዮጵያዊ የዜግነት ማንነት ገንብተዋል፣አንዲት ኢትዮጵያ የምትባል አገር መሥርተዋል፣ የነዚህ መታወቂያና መለያ የሆነ፣ አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ቀለም መለያው የሆነ ሰንደቅ ዓላማ ባለቤት ሆነዋል የሚለው ተፃራሪ የሆነው፣ የኦነግ ዓላማ አራማጅነት እንደሆነ ያሳያል። ኦነግ ምኒልክን «በቅኝ ገዥነት፣በጡት ቆራጭነት፣ በጥቁር ናዚነት» እንደሚከስና አዲስ አበባን «ፊንፊን» እንደሚል ይታወቃል። እናም ኤፍሬም ፊንፊኔ ብል በቀጥታ ኦነግ አድርገው ይስሉኛል፣ ለዚህ ሸገር ብል አምታትቸ አልፋለሁ ብሎ አዲስ አበባን በሸገር ተክቷል። በሌላ በኩል ድርጅቱ ከተለያዩ ተገናጣይ ቡድኖች ጋር አደረኩት በሚለው ኅብረት፣ አንድነት፣ ጥምረት ወዘተ የኦነግን አገራዊ መለያ ምልክት በየስብሰባው አዳራሽ ሲያውለበልቡ ይታያሉ። ይህም የኢትዮጵያን አንድነት ያመጣል ተብሎ አይታሰብም።

ኤፍሬም ፈሪ መሆኑን የበለጠ የሚገልጸው እንዲህ በማለት ነው። «ደሞኮ የፍርሀት ነገር ሆኖ ነው እንጂ፣ሰው በሁለት ግዙፍ ሰማያዊ አካላት መካከል እየበረረ ይፈላሰፋል እንጂ፣ እንዴት ይፈራል? ወይ ፍርሀት--- ፍርሃት መጥፎ ነገር ነው፤» በማለት የፍርሃቱን መጠን ይነግረናል። አያይዞም በፍርሐት የተያዙ ሰዎች የሚያሳዩትን ባሕሪ እንዲህ ሲል ያብራራዋል። «ሰው ሲፈራ የሚወደውን ነገር ይጠላል፤ ሰው ሲፈራ የናቀውን፣ ያዋረደውን ያከብራል፤ ሰው ሲፈራ ሕይዎቱን ረግጦ ለሚገዛው ይሰግዳል፣ ሰው ሲፈራ ነፃነቱን የቀማውን ጎንበስ ብሎ ያገለግላል፤ ሰው ሲፈራ ሕይዎቱን ተቀምቶ ኑሮ ይናፍቀዋል።» ይልና ፍርሐትን ማስወገድ እንዳለብን ይማጸናል።
እነዚህን አገላለፆች ገልብጠን ብናነባቸው፣ ኤፍሬም ይወዳት የነበረችው የመጀመሪያ የሴት ጓደኛው፣አስመራ ሲገባ ድሮ ትውደው እንደነበር እንደማትወደው እና እንደጠላችው፣ (ልብ በሉ ባንድ ወቅት ኤፍሬም ከዩኒቨርሲቲ ትምህርቱ እንደጨረሰ ኤርትራ/አሥመራ ለሥራ ተመድቦ የመጀመሪያ ሴት ጓደኛው ኤርትራዊት እንደነበረችና በጣም ይዋደዱ እንደነበር ነግሮናል)፣ ድሮ ሻዕቢያን ይንቀው፣ያዋርደው እንደነበር፣ አሁን ግን እንደሚያከብረው፣ማክበር ብቻ ሳይሆን፣ እንደሚፈራው፣ እንቅስቃሴው በሻዕቢያና በኢሳያስ ቁጥጥር ሥር በመውደቁ ረግጦ ለያዘው ሻዕቢያና ኢሳያስ የሚሰግድ መሆኑን፣ለነፃነቱ ነጣቂ ሻዕቢያ አጎንብሶ እየሰገደ እንዳለ የሚያሳይ ነው። በአጠቃልይ፣ በእርሱ ላይ የነገሠ የፍርሃት ቆፈን በሁሉም ላይ የነገሠ መስሎት፣ ፍርሃትን እናስወግድ ይለናል። ጥያቄው መልካም ነው። ግን ፍርሃትን ፈጽሞ ማስወግ እንዴት ይቻላል ? ፍርሐት ተፈጥሮአዊ ነው። ፍርሐት የአዕምሮአችን አንዱ አካል የሆነ፣ እንቅስቃሴአችን አደጋን ጋባዥ የሆነ ሁኔታ ሲፈጠር ከዚያ አደጋ ለመውጣት ማድረግ የሚገባንን ድርጊት ሁሉ እንድናደርግ በሚልከው መልዕክትና በሚያመነጨው ሆርሞን፣ የተነሳ የሚፈጠር ከአደጋ የማምለጥና የመዳን አጣዳፊ አካላዊና አዕምሮአዊ እንቅስቃሴ ነው። ይህ እንቅስቃሴ ነው ጀግንነትን የሚወልደው። ስለሆነም ፍርሀትን ማስወገድ ሳይሆን፣ ፍርሐት ከሚፈጥሩ ተግባሮች ራሳችን ማራቅ፣ ፍርሃት የሚፈጥሩ ነገሮችን አውቆ ማስወገጃ ስልቱን መቀየስ፣ ፍርሀት ጀግንነት የሚወልድበትን ሁኔታ ማመቻቸት ግን ይቻላል። ፍርሃትን ሳታስወግድ አስመራ መሽግ ብሎ ያስገደደህ ማነው? ብርሃኑ? አንዳርጋቸው? ማንኛው ነው?

2 ኤፍሬም «የኦዞ ኢትዮጵያውያን ማንነታቸውን በኢትዮጵያዊነት ውስጥ የሚታዩ አስተዋይና አርቆ አሳቢ ሰዎች እንጂ፣ የዘውግና የክልል እስረኞች አይደሉም» ይላል። በወገናቸው ላይ ዓለም ያወቀው ፀሐይ የሞቀው የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል በተፈጸመበት ዐማራ ፣ ባለፉት 25 ዓመታት ብቻ ከ 5 ሚሊዮን በላይ ከምድረ-ኢትዮጵያ የጠፉበት፣ የመዋለድ ተፈጥሮአዊ መብቱ ተነጥቆ ትውልድ አልባ የሆነ፣ በኢትዮጵያ ምድር ሠርተህ አትኖርም የተባለና በግፍ ሀብት ንብረቱን ተነጥቆ ለልመናና ላሰቃቂ ኑሮ ለተዳረገው ወገናቸው የጎልውና ጥያቄ አንስተው የሚጮኹትን ወገኖች፣«የዘውግና የክልል እስረኞች» ሲል ይከሳቸዋል።
አውትራሊያን ደጋግሜ ባላየውና የነዋሪዎቹን ማንነትና ስብጥር ጠንቅቄ ባለውቅ ኖሮ፣ ይህ የኤፍሬም የበሬ ወለደ አባባል ምናልባች ጎሊናየን አጠራጣሪ ሁኔታ ላይ ሊጥለው ይችል ነበር። ኤፍሬምን ለመቀበል በየአዳራሹ የተገኙ የራሱ ዘውግ አባሎችና የግንቦት 7 አባሎች ብቻ እንደሆኑ ዝርዝር ሪፖርቱ አለኝ። ዐማራው ዘውገኛም ክልለኛም አይደለም። ራሱ

«ክልል» የሚለውን ቃል፣ ወያኔን መንግሥት ብሎ የመጥራትና የወያኔን ሕገ መንግሥትና በቋንቋ ላይ የተመሠረተውን መንግሥታዊ አደረጃጀት ዐማራው አላጸደቀም። አልተቀበለውም። ይህን ተቀብሎ የሚያስተጋባው ኤፍራምና ልሳኑ ኢሣት ናቸው። ይህን ሕዝብ ያውቃል። ዐማራው በሽግግር መንግሥቱ ጉባዔ አልተወከለም። የተወከሉት የኤፍሬም ዘመዶች፣ እነ ተስፋዬ ሐቢሶ፣ ዶ/ር ኃይሌ ወልደሚካኤል፣ እነዶ/ር በየነ ጴጥሮስ፣ እነአሰፋ ጫቦ፣ መኮንን ዶሪ፣ ፋንታሁን ኃይለሚካኤል፣ ቴዎድሮስ ኤፍሬም፣ ገብሩ ጴጥሮስ፣ ወልደሚካኤል ዱባለ፣ በተና ሆቴሶ፣ አልታየ አላሮ፣ ሰይፉ ቡቄ፣ ዲማ ነገዎ፣ ሌንጮ ለታ፣ገላሳ ዲልቦ፣ አቢዩ ገለታ፣ ሐሰን ዓሊ፣ አባዱላ ገመዳ፣ ኩማ ደመቅሳ ወዘተ ወዘተ መሆናቸው ይታወቃል። ዐማራው አገር ሲገነባ፣ አንድነት ሲያጠና እንጂ፣ አገር ሲያፈርስና ዘውግን ሲያቀነቅን አይታወቅም። ኤፍሬም ማዴቦ ምኒልክን ከመለስ ጋር አንድ አድርገህ ሁለቱም አገር አጠፉ ስትል የጻፍክ ሰው፣ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ለምኒልክ ልጆች፣ ልታስተምር የሚያስችል ድፍረቱም ሆነ ወኔው የለህም። የምኒልክን አገር ገንቢነት እና ራዕይ ያልተቀበለ ሰው በቴዎድሮስ ኢትዮጵያያዊነት ሊያምን ይችላል ተብሎ አይታሰብም። ምክንያቱም ቴዎድሮስ ምኒልክ፣ ምኒልክ ቴዎድሮስ ናቸው። ሁለቱም ካንድ ሕዝብ አብራክ የወጡ፣ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ጥልቅ ራይዕ የነበራቸው፣ ይችን ያንተና የድርጅትህ ጌታ የሆነው ሻዕቢያ የበጣጠሳትን አገር፣ አገር አሰኝተው፣ መሠረትና ጭምጭም፣ ማገርና ወራጅ፣ ምሰሶና ካስማ ሠርተው ያለፉ ጀኖች ናቸው። ዓለም ያደነቃቸው፣ አገርና ሕዝብ አዘማኝ የዐማራው ብቻ ሳይሆን፣ የጥቁር ሕዝብ ዕንቁዎች መሆናቸውን ኤፍሬም አይቀበልም። ይህን ያልተቀበለ በነዚህ ሰዎች ራዕይነት የሚጓዙ ሰዎችን ዘውገኛና ክልለኛ ብሎ መውቀስ እንዴት ይቻለዋል? «የእምየን ወደ አባየ ልክክ» ይሏችኋል ይህ ነው።

3 «ወያኔን ማሸነፍ የምንችለው በኢትዮጵያዊነት ነው» ይለናል። ኢትዮጵያዊነት መንፈስ፣ የዜግነት መገለጫ እንጂ፣ ድርጅት አይደለም። ወያኔን የምናሸንፍው፣ኢትዮጵያዊ በመሆናችን ብቻ ሳይሆን፣ ከብረት የጠነከረ ድርጅት፣ በኢትዮጵያ ጥንታዊ አገርነት የምናምን፣ በዐምደጽዮን፣ በዘርዓያዕቆብ፣ በዳዊት፣ በናዖድ፣ በሰርፀድንግል፣ በገላዲዎስ፣ በሚናስ፣ በፋሲል፣ በቴዎድሮስ፣ በምኒልክ፣ በቀኃሥ የኢትዮጵያ ነገሥታት መሆን አምነን፣ የእነርሱን ራዕይ ለማስቀጠል በሚኖረን ቁርጥጠኝነትና ድርጅታዊ ብቃት ነው። ይህን ሳናምንና ሳንቀበል፣ ከሁሉም በላይ ዐማራውን በጠላትነት ፈርጀን ለማጥፋት እየጣርን ኢትዮጵያዊ ነን ለማለት የምንችልበት መሠረት የለንም። በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያዊነትን ክዶ በዘር ማን እንደተደራጀ የሽግግር መንግሥት ምሥረታው የተሳተፉና በኋላም ያሉትን ድርጅቶች ማየት ነው። ለኤርትራ መገንጠል ዕውቅና ሰጥቶ፣ ኤርትራን ምሽጉ ያደረገው ማን ይሆን? የቀይ ባሕርን የኢትዮጵያን የተፈጥሮ በርነት ፈቅዶ የሰጠው ከመለስ ቀጥሎ ማነው እንበል? ኤፍሬም ወይስ ብርሃኑ? ወይስ ግንቦት 7? ይህ ዐማራን በክልልና በዘውግ የመክሰስ ጉዳይ፤ «ከሣሽ ተከሳሽ የሚለውን ቢያውቅ ኖሮ፣ ለክስ አደባባይ አይወጣም ነበር» የሚለው አባባል ለኤፍሬም ከበቂ በላይ መልስ ነው።

4 «ሜልበርን ቤታቸው ሂጀ ያጫዎቱኝ አባት፣``ልጀ የቴዎድሮስ ዘር ነኝ እያለ የሚሰብከውን ውሸታም ሁሉ፣ አደራ እንዳታምነው፤ ቴዎድሮስ የአንድነት እንጂ፣ ልዩነትን አልሰበከም።» ብለው እንደመከሩት ጽፏል። ከዚህ ላይ አንባቢዎቸ ልብ በሉልኝ። የውሸት ነገር ከተነሳ ምንጩ ከየት ይሆን? የአዳፍኔ ምስክር የት አካባቢ ይሆን? በታሪካችን ሰዎች ያላዩት አየን፣ ያልሰሙትን ሰማን በማለት በሀሰት የሚመሰክሩ ሰዎች በብዛት ይገኙ የነበረው የትኛው አካባቢ ነበር? በፍርድ አደባባይ በሀሰተኛው ሙብዛት የተነሳ ለአንድ ሰው ምስክርነት አምስት ሰዎች ወይም አምስት ሰዎች እንደ አንድ ሰው እንዲመሰክሩ የተደረገበት አካባቢ የት ነበር? የቴዎድሮስ ዘሮች ሃይማኖተኞች፣ ለማተባቸው ጽኑዎች፣ ለወገናቸው ተቆርቋሪዎች፣ ለአገራቸው አንድነትና ነፃነት ቀናዒዎች እንጂ፣ በአፋቸው ጨው የሚሟሟ አይደሉም። ኤፍሬም ይህን ነገሩኝ ወይም መከሩኝ ያላቸውን አዛውንት ማንነት ቢጠቅስልን ኖሮ፣ አባባሉ ትንሽ ወደ ተባለው ነገር ሊጠጋ ይችላል ብለን እንድናስብ ግፊት ሊያደርግብን ይችል ነበር። ግን ልብ ወለድ ስለሆነ ስማቸውን አልጠቀሰም። እናም አባባሉ የራሱ ፈጠራ ከመሆን አይዘልም። ከሁሉም የሚገርመው አንድነት እና ኢትዮጵያዊነት ሲነገር የሚያንገሽግሻቸው እና አየር የሚያጥራቸው ግንቦቴች ሆነው ሳለ፣ ጎንደሮች፣ ጎጃሞች፣ ሸዌዎች፣ ወሎዮች በጥቅሉ ዐማሮች አንድነትና ኢትዮጵያዊነትን ከሌሎች ይማራሉ ማለት ሸንበቆ ያፈራል፣ በቅሎ ትወልዳለች፣ ገለባ ያብባል እንደማለት ነው። ይህን ትምክህትና ማንአህሎኝነት እንደሚባል ይገባኛል። አዎ! ማን አህሎን! የሚመካም ያለው፣ የተናገረውን ያለውን የማድረግ ብቃት ያለው ነውና ትምክህተኛ ነኝ።

ኤፍሬም ለወገናቸው ኅልውና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚጮሁ ወገኖችን፣ «እንደዛሬዎቹ የእርሳቸው (የቴዎድሮስ) ልጆች ነን ባዮች፣ቋንቋና ዘርን አልሰበኩም።» በማለት ይከሳል። ዐማሮች የቴዎድሮስ ልጆች እንዳልሆኑ «ነን ባዮች» ሲል

ሊያሳንሳቸው ይቃጣል። ግንቦት 7 በዐማራው ላይ የገነባው ጥላቻ የቱን ያህል የከፋና የከረረ መሆኑ ማሳያው የሚከተሉት ናቸው።

(ሀ) የግንቦት 7 አመራር አባል ለመሆን ከአማርኛ ውጭ ሌላ ቋንቋ የሚናገር መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። ይህም ማለት አማርኛን ሲያልፍ በየመንገዱ ማንም የሚናገረው የወል ቋንቋ ነው። ይህም የግንቦት 7 ን ማንነት አይገልጽም። የግንቦት 7 ን ማንነት ለመላበስ ወይም ለመሆን፣ ዛሬ ደቡብ ተብሎ በተደራጀው የኢትዮጵያ ክፍል ከሚኖሩ ከ 45 በላይ ነገዶች የአንዱ አባል የሆነ፣ ያን ቋንቋ የሚናገር መሆን አለበት። ይህ ሲሆን ብቻ ነው የግንቦት 7 መገለጫ። አማርኛ መናገር ለዚህ ድርጅት መገለጫውም መታወቂያውም አይደለም። ባዕድ ነው። ግንቦት 7 ዐማራውን የሚፈልገው የገጠሩን ለወታደርነት፣ ለጦርነት ነው። ከተሜውን ዐማራ፣ ለገንዘብ፣ ለወንበር ድርደራ፣ ለስብሰባ አድማቂነት ነው። ከዚህ ውጭ በውሳኔ ሰጭነትና ሀሳብ አፍላቂነት ኢትዮጵያዊነትን ስለሚያስቀድም አይፈለግም። ለዚህም በአመራሩ ውስጥ አንድ ዐማራ ተፈልጎ አይገኝም። አለን ካሉም በእሳት ውስጥ እንዳሉት ኤርትራውያን ወይም ይኸን ያህል በመቶ ዐማራ ነን የሚሉ ናቸው። እነዚህ ደግሞ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ የቱን ያህል እንደሚሆን አምላክ ይወቅ።

(ለ) በግንቦት 7 ልሣን በሆነው ጋዜጣቸው ቁጥር 25 ጥቅምት 2001 ዓም ርዕስ አንቀጽ፣ ለ 250 ዓመታት በነጮች ሲገዙ የነበሩት ጥቁሮች ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት ከበቁ፣ እኛም ለአሥር ሺ ዓመታት በዐማሮችና በትግሮች ስንገዛ የኖርነው ኦሮሞዎችና ደቡቦች የኢትዮጵያ መሪዎች እንሆናለን፣ በማለት የገለጹት፣ ዐማራውን በገዥ እና ጨቋኝ ብሔረሰብ ፈርጀው ለመበቀል የተደራጁ መሆኑን ያሳያል።

(ሐ) የግንቦት 7 ሊቀመንበር ብርሃኑ ነጋ፣ ከእስር ተፈትቶ አሜሪካና አውሮፓ እንደገባ ለምን ቅንጅትን አፈረስክ ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ፣ የሰጠው መልስ ትግሬ አውርጀ ዐማራ ሥልጣን እንዲይዝ ባለመፈለጌ ነው ማለቱ ይታወሳል። ከእሥር እንደተፈታ የእሥር ጓደኞቹን ተለይቶ ገሥግሶ የገባው ከኦነግ ጋር ግንኙነት ለመመሥረት የሚያስችለውን መሥመር ለመዘርጋት ወደ ዱባይ እንደሆነ ይታወቃል።

(መ) «የደራሲው ማስታዎሻ» በሚል ርዕስ የሻዕቢያው ሰላይ ተስፋዬ ገብረአብ የጻፈውን ዐማራን፣ ምኒልክንና ቴዎድሮስን በአጠቃላይ የኢትዮጵያዊነት የወል ዕሴቶችን አራክሶና እንዳልነበሩ አድርጎ የጻፈውን፣ ያሳተመው ንብረትነቱ የግንቦት 7 የሆነው «ነፃነት አሳታሚ» ነው።

ይህንም ትውልድ አጥፊ መጽሐፍ ብርሃኑ ነጋ እንዲህ ሲል በሽፋን ገጹ ላይ አድናቆቱን ሰጥቷል።

« ባለፉት 40 አመታት የፖለቲካ ስነጽሁፍ ተቀብሮ ከነበረበት፣ ተስፋዬ ገብረአብ ራሱም ባንድ ወቅት ተዘፍቆበት ከነበረው እንጨት እንጨት ከሚል የካድሬ ፖለቲካ መሳሪያነት አውጥቶ አድማሳዊ የሆኑ ሰብአዊ እሴቶችን መፈተሻ በማድረግ ነፍስ ሊዘራበት የጀመረው ሙከራ እየተሳካ ለመሆኑ `` የደራሲው ማስታዎሻ `` በቂ ምስክር ነው » ይላል ። ይህም ብርሃኑ ይህን ምስክርነት ሲሰጥ፣ ለተስፋዬ አድናቆቱን የሰጠው በጋራ የሚጋሩትን በመጽሐፉ በእያንዳንዱ ርዕስ ዐማራና ኢትዮጵያዊነትን ጥላሸት ስለቀባለት ነው።

5 «የቴዎድሮስ ትልቅነትና ዐዋቂነት ይዞት የተነሳው ራዕይ እንጂ፣ የተወለደበት ቦታ አይደለም።» ኤፍሬም ይህን ሲል ቴዎድሮስን ከነባራዊ ሁኔታ ውጭ ያየው ይመስላል። ዝም ብሎ ትልቅነት አይገኝም። ትልቅነት ማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኝ ፖለቲካው፣ኢኮኖሚያዊ ፣ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሁኔታዎች መስተጋብር የሚፈጥሩት ነው። ሃይማኖት የተስፋፋበት አካባቢ የተወለዱ ሰዎች ሃይማኖት አስተማሪዎች ባይሆኑም፤ ስለሃይማኖት ግንዛቤ ይኖራቸውል።

የሃይማኖትንም ሥርዓት ከሌሎች በተሻለ ያውቃሉ። ጦርነት በተደጋጋሚ በሚካሄድበት አካባቢ የተወለዱ ሰዎች ስለጦር መሳሪያ አጠቃቀም፣ ስለጦርነት ጉዳትና ጥቅም ከሌሎች የተሻለ ያውቃሉ። በጥቅሉ የገበሬ ልጅ ግብርና፣ የሸማኔ ልጅ ሽመና፣ የአንጥረኛ ልጅ፣ ብረት ማቅለጥ፣ የነጋዴ ልጅ ስለንግድ ከሌሎች በተሻለ ያውቃሉ። ይህም ሰዎች የሚገኙበት ነባራዊ ሁኔታ የነርሱን የወደፊት ማንነት ይቀርጻል። በመሆኑም ቴዎድሮስ ያን ለመሰለ ታላቅ አገራዊ ዕራይ ሰንቀው እንዲነሱ ያደረጋቸው፣ በተወለዱበት አካባቢ የነበረው የሕዝብ አስተዳደርና አኗኗር፣ ባህልና ፖለቲካዊ ሕይዎት የቀረጻቸው ናቸው። ይህም በመሆኑ ቴዎድሮስ ጎንደር ለኢትዮጵያ አንድነት ትንሣኤ ያበረከተቻቸው ዕንቁየ መሪ ናቸው። ያለቦታ ታላቅም ሆነ ታናሽ አይወለድም። ሰውየውን ከቦታው፣ ቦታውን ከሰውየው ነጥሎ ማየት የተሟላ ሥዕል ሊሰጠን አይችልም።

ቴዎድሮስ ሙሉ

የሚሆኑት ከተነሱበት ጎንደር (ቋራ/ደንቢ) ከተጓዙበት ጉዞና ከኖሩበት ማኅበረሰብ ጋር ተጣምረው ሲታዩ ነው ታላቅነታቸው ጎልቶ የሚወጣው። ካለበለዚያ ነጠላ ይሆናሉ። ቴዎድሮስ እጥፍ ድርብ ማንነት ያላቸው ናቸውና!

ዐማራን በጠላትነት ፈርጀ፣ አዋርዶና ንቆ ከዐማራው ገንዘብም ሆነ ሌላ ድጋፍ ለማግኘት መመኘት አንድም ዐማራውን መናቅ ነው፣ ሌላም ዐማራው ስለማንነቱ የማይጨነቅ ከብት ነው ብሎ እንደማሰብ ይቆጠራል። ላለፉት 9 ዓመታት ዐማራው በኢትዮጵያዊነቱ ባለው ጽኑ ዕምነትና አድሮ እንየው በሚለው ባህሉ፣ ያየውን እያየ፣ የሰማውን እየሰማ ግንቦት 7 ን ተከትሏል፤ አጅቧል። ከሐምሌ 5 ቀን 2008 ዓም ቀን ጀምሮ ግን ለካ! ብሏል። አፈርኩ ብሏል። ይህን ባህሉን ላወቀ በቃን ማለቱ ነው። ዐማራውን ጠላቴ ነው ብሎ በስስና ልባዊ እምነቱ በኢትዮጵያዊነት ስም የሚነገደውን ንግድ አወኩባችሁ ብሏል። «ሞኝ ካመረረ፣ በግ ከበረረ» መመለሻው ዕሩቅ ነውና በዚህ በኤፍሬም ሽንገላ የሚመለስ አይሆንም። ከድፍን ኢትዮጵያ የለህም ወዳጄ፣ ዐማራ ዐማራውን መጠበቅ ነው እንጂ፤ ብሎ ጎልውናውን ለማስጠበቅ ቆርጧልና በቴዎድሮስና በኢትዮጵያዊነት ስም ለዳግም ክዳት ክንዱን ኅሊናውን አይሰጥም። የማያፈራ ዛፍም አይንከባከብም። ኤፍሬም ማዴቦ ደጋግሞ ስለፍትሕና እኩልነት አንድነት አውስቷል። ኤፍሬም አንድነት ፣ፍትሕ፤ ዕኩልነት ሲል ዐማራውን እንዲጨምር አድርጎ እንዳልሆነ ድርጊቱ ያሳያል። እንዲህም ይለናል። «እኛ ኢትዮጵያውያን እንደዚህ ዓይነት ጠንካራ መርህ እንዲኖረን የግድ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ሆኖ መፈጠር የለብንም።ኢትዮጵያ ከምትባል አገር ውስጥ ሰው ሆነን መፈጠር ብቻ ነው ያለብን።» ይህ አጠቃላይ ዕውነት ነው። ግን ዐማራው ኢትዮጵያ ውስጥ አልተወለደም ወይ? ዐማራው ፍትሕ፣ ዕኩልነት ቀርቶ በአገሩ የመኖር መብት አለው ወይ? ዛሬ ለዐማራው ድምፅ እየሆኑ ያሉ ወገኖችና ኤፍሬም በዘውግ አራማጅነት የሚከሳቸው፣ በምሥራቅ እና በምዕራብ ሐረርጌ፣ በአርሲ አርባጉጉ፣ በምሥራቅ ወለጋ፣ በኢሉባቡር፣ በጃዊ፣ በመተከል፣ በጉራ ፈርዳ፣ በወልቃይት ፣ጠገዴ፣ ጠለምትና አርማጭሆ፣በራያና ቆቦ ይኖሩ በነበሩ ዐማሮች ላይ፣ ከዘር ማጥፋት እንስከ ዘር ማጽዳት ወንጀል ሲፈጸምባቸው እንደ ድርጅት ግንቦት 7፣ እንደ ዜና አውታር ኢሣት መግለጫ ሊያወጡ ቀርቶ፣ ሞረሽ ወገኔ ያወጣቸውን የአገዛዙን ገመና የሚያጋልጡ ሐቆችን ለመዘገብ አልሞከሩም።

ከሁሉም በላይ በተስፋዬ ገብረአብ የተጻፈው «የቡርቃ ዝምታ» የተሰኘ ፀረ- ምኒልክና ዐማራ የሆነው የሻዕቢያ የፈጠራ ድርሰት ዕውቅና ተሰጥቶት አገዛዙ የኦሮሞና የዐማራ መጭ ትውልዶች ጎን ለጎን እንዳይቆሙ፣ ዓይንና ናጫ ሆነው የወያኔን አገዛዝ ከማስረዘም አልፎ፣ ኢትዮጵያ እንድትበታተን ዕውቅና የሰጠውን «የአኖሌ ሀውልት» የተሰኘ፣ በመሀል መዳፍ ላይ የተቆረጠ ጡት የተቀመጠበት ሀውልት በይፋ አርሲ ላይ ሲገነባ፤ግንቦት 7 ም ሆነ ኢሣት ያሉት አንዳችም ነገር የለም። ይህን በተመለከተ የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ የአማርኛው ክፍል አገልግሎት ዶ/ር ኃይሌ ላሬቦን፣ ዶ/ር ሹመት ሲሻኝን እና አቶ ቡልቻ ደመቅሳን አነጋግሮ ነበር። ሁለቱ የታሪክ ምሁራን ምኒልክ በዚያ ቦታ የኦሮሞ እናቶችን ጡት ስለመቁረጣቸው የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩን ሲገልጹ፣ ቡልቻ «ምኒልክ የኦሮሞን እናቶች ጡት ቆርጧል፤ ምኒልክ የጥቁር ፋሽስት ነው» ሲል የታሪክ ዕውቀቱን ሳይሆን፣ የፖለቲካ አቋሙን መናገሩን እናስታውሳለን። ይህን ተከትሎ እኔ ተክሌ የሻው ኢሣት ቢሮ ሂጀ፣ ስለአኖሌ ሀውልት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እየተጋበዙ ሐቁ ከሀሰቱ፣ ፖለቲካው ከታሪክ፣ ፈጠራው ከነባራዊ ተለይቶ እንዲታወቅ ፕሮግራም በሥሩት እንዲሠራ ላቀርብኩላቸው ጥያቄ፣ የወቅቱ የኢሣት ሥራ አመራር ኃላፊ የነበረው ነዓምን ዘለቀና ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን ባንድ ድምፅ «እኛ እኮ ኦሮሞ ነን» በማለት ዕውነቱን ለሕዝብ ለማሳወቅ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ስለዚህ ጉዳይ ኢሣት ዘግቧል የሚል ካለ መረጃውን ለማየት/ለመስማት ዝግጁ ነኝ። ማንም እንደሚገነዘበው ኤፍሬም ማዴቦና ዶ/ር ላጲሶ ጌ ድሌቦ የአንድ ነገድ አባል ባይሆኑም፣የአንድ አካባቢ ሰዎች ናቸው። ላጺሶ በፋሲል የኔዓለም ጠያቂነት ረጅም ሰዓት ተሰጥቶት፣ ዐማራን፣ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን፣ ምኒልክን ፣ ነባርና ተያያዥ የኢትዮጵያዊነት የወል እሴቶችን፣ የሕዝቡን አኗኗርና ታሪክ ተረት ተረት ናቸው። የኢትዮጵያ ታሪክ እንደገና መጻፍ አለበት ሲል ለቀባጠረው አጻፋ ለመስጠት፣ ጋዜጠኛውን ጠይቄ ፈቅዶልኝ ባደረግነው ውይይት፣ ከሙያው ሥነ-ምግባር በወጣ መልኩ እኔን ያሳነሰኩ፣ ላጺሶን ያሳደገ መስሎት፣ እርሱ እንደነገረንም ሚስቱ እስከምትስቅበት ድረስ የወረደ፣ በግንቦት 7 እና በኢሣት አመራሮች የተሰጠውን የቤት ሥራ ለመወጣት ያደረገው የተወላከፈ ተግባር ፕሮግራሙን ያዳመጡና ያዩ ያውቁታል። ይህ በኢሣት ዝግጅት ላይ የፈጠረው አሉታዊ ተጽዕኖ ማየል የተነሳ፣ የዝግጅት ክፍሉ ፋሲል እኔን ይቅርታ እንዲጠይቅ ያዘዋል። ፋሲልም በታዘዘው መሠረት ደውሎ ስለሁኔታው በማውሳት ይቅርታ አድርግልኝ ይለኛል። እኔም ይቅርታ መጠየቅ ታላቅነት ነው። መልካም አልኩት። ይህን በአየር ላይ አውለዋለሁ አለኝ። እኔ ስንነጋገር እየቀዳ መሆኑን አላውቅም ነበር። እርሱም የሚቀዳው መሆኑን አልነገረኝም ነበርና፣ ይህማ አይሆንም። ይቅርታው በእኔና ባንተ ብቻ ይበቃል ስለው፣ የለም በዚህ የተነሳ በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ ስለተነሳ ይቅርታውን ሕዝብ መስማት አለበት

አለኝ። ጉዳዩ ይህ ከሆነና ይቅርታው በአየር ላይ እንዲውል ከፈለክ በእኔና በአንተ መካከል አንድ ሰው መኖር አለበት። ያ ሰው ስለጉዳዩ አብራርቶ የአንተን ይቅርታ ጠያቂነት፣የእኔን ይቅር ባይነት ማሳየት አለበት አልኩት። እርሱም በሀሳቤ ተስማምቶ ማን ቢሆን ትመርጣለህ አለኝ። እኔም አቶ ሢሣይ አጌናን እመርጣለሁ አልኩት። በዚህም ተስማምቶ ተለያየን። ብዙም ሳይቆይ ሢሣይ ደወለልኝ። በእርሱ አማካኝነት ፋሲል፣ እኔን ይቅርታ እንደሚጠይቅ ነግሮኝ ቀጠሮ ያዝን። በቀጠሮ ቀን ሁለቱም ጠፉ። ደወልኩና ምነው አልኩት ሢሣይን። ሁኔታውን እያመቻቸን ነው በቅርብ ቀን ይሆናል አለኝ። ጠበኩ፤ የውኃ ሽታ ሆነ። በመሐል አንድ ሲያትል እንደሚኖር የተነገረኝ ሱራፌል የሚባል ሰው ኢሜል ደረሰኝ። የኢሜይሉ መልክዕት«ኢሣት ተክሌን ይቅርታ ቢጠይቅ ካለፈው የከፋ ጉዳት ያደርሳልና ባይጠየቅ ይሻላል »የሚል ነው። ይህንም ለሢሣይ እንዲያውቀው ብየ ላኩለት። መልስ የለም። እንግዲህ ልብ በሉ፣ ስለፍትሕና ኢትዮጵያዊነት፣ ስለቴዎድሮስና ዕኩልነት የሚነግረን ኤፍሬም ማዴቦ ይህን የመሰለውን ኢፍትሐዊ ሥራ እየሠራ ነው።

6 «ዛሬ እንደዚህ ዓይነቶቹ ትላልቅ የኢትዮጵያዊነት እሴቶች ተረስተው በአንዳንድ የፖለቲካ መድረኮች ላይ በአገር መውደድ ስም ብሔርተኝነት እየተሰበከ ነው። ይህ አደገኛ ስብከት አገራችን የምትገኝበትን ሁኔታ በሚገባ አለመረዳት፣ከግድ የለሽነት፣ለራስ ጥቅም ከመቆምና አገር ወዳድነትና ብሔርተኝነትን ለያይቶ ካለማየት የሚመጣ ፣በጊዜ ካልታከሙት የማይድን በሽታ ነው። በአገር ወዳድነትና በብሔርተኝነት መካከል የሰማይና የምድር የሚያክል ትልቅ ልዩነት አለው።አገር ወዳዶች ሰዎችን ለያይተው የሚያዩበት መነጽር የላቸውም። አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚመለከቱት እንደወገናቸው ነው።»
ሁሉም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን፣ ዐማራንና የኢትዮጵያዊነት የወል ዕሴቶችን ለማውደም የጣሩ፣ ዐማራን በዘር ለይተው ለማጥፋት ብዙ የደከሙ ሁሉ፣ የመጨረሻ ቀናቸው ላይ ኢትዮጵያዊነትን ሙጥኝ እንደሚሉ ከታሪክ ብቻ ሳይሆን፣ ከዛሬ የኢትዮጵያ ፖለቲካ በግልጽ እያየን ነው። የወያኔ ትውልድ የኢትዮጵያን ታሪክ መቶ ዓመት አይሞላም፣ በምኒልክ የተጀመረ ነው ፣እንዳላለ ሁሉ፣ ዛሬ ከማንም በላይ ኢትዮጵያዊ ነኝ እያለን ነው። መለስና ሟቹ አቡነ ጳውሎስ የኢትዮጵያ ታሪክ ከሦስት ሺ ዘመን በላይ መሆኑን በኢትዮጵያ ሚሊኒየም የዘመን አለዋወጥ ሥነሥርዓት ሲናገሩ ሰምተናል። ኢትዮጵያዊ አይደለንም፣ በዐማራ ቅኝ ተገዝተናል፤ ከኢትዮጵያ ተገንጥለን ኦሮሚያ የሚባል አገር እንመሠርታለን በማለት የኦሮሞን ወጣት በሀሰት ድርሳን ሲሰብኩ የነበሩት እነሌንጮ ለታ(ዮሐንስ ለታ)፣ዛሬ ኢትዮጵያዊ ነን እያሉን ነው። የኤፍሬም ማዴቦም ኢትዮጵያዊነት መዝሙር፣ «ሲፋጅ በማንካ፣ ሲበርድ በእጅ» እንዲሉ፣ ግንቦት 7 በዐማራው ነገድ ላይ በሠራው አድላዊና አግላይ ፖለቲካ ፣ዐማራው ይሄም አለን እንዴ ብሎ በማንነቱ ዙሪያ ተደራጅቶ፣ ኀልውናውን በአስተማማኝ ሁኔታ ካረጋገጠ በኋላ፣ የኢትዮጵያን አንድነት ከሚያምኑና ከሚቀበሉ ሌሎች ነገድና ጎሳ ድርጅቶች ወይም ኅብረ ብሔራዊ ድርጅቶች ጋር በማበር እናረጋግጣለን በመለቱ፣ ለግንቦት 7 እና ለኢሣት ያፈስ የነበረውን መዋጮ በማቆሙ ምክንያት፣ ችግር የገባው ኤፍሬምና አመራሩ ስለኢትዮጵያዊነት እኛ ሊሰብከን ይሞክራል። «ለቀባሪው ማርዳት» ማለት ይህ ነው።

ግንቦት 7 በኢትዮጵያዊነት ቢያምን ኖሮ፣ የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ከተባለው ድርጅት ጋር ውሕደት ፈጸምኩ ሲል፣ «ኢትዮጵያ» የሚለውን ስም ውድቅ አያደርገውም ነበር። ግንቦት 7 ዐማራው ከመጥላት ዘሎ የናቀው መሆኑ ማሳያው፤ ምሽጉን ኤርትራ አድርጎ፣ በትጥቅ ትግል ጎንደር፣ ጎጃምን እና ሸዋን ረግጦ አራት ኪሎ ለመግባት «ትልቅ ዕቅድ» አለኝ የሚል ድርጅት በአመራሩ ዐማራ የለም። ማንነቱን ሳያውቁ መሥራች አባላት ሆነው የነበሩት እነ መሥፍን አማን፣ ጋሻው ካሤ፣ አገኘሁ መኮንን፣ አንተሁን ሙሉጌታ በተለያዩ ምክንያቶች ከድርጅቱ እንዲባረሩ ተደርገዋል። ተባረውም ዲ-ግንቦት 7 የሚል ቡድን መሥርተው የድርጅቱን ሤራ ማጋለጣቸው ይታወቃል። ኢትዮጵያ የሚለውን እና አንድነትን ቀድሞ የጠሉ ወገኖች፣ ዛሬ ሁኔታዎች ከነርሱ እሳቤ ውጭ ሲሆን፣ ስለኢትዮጵያነት የመስበክ ሞራሉን ከየት ተዋሱት? የዐማራውንስ ኢትዮጵያዊነት በምን ሁኔታ ተጠራጠሩት?

ኤፍሬም «አደገኛ ነው፣በጊዜ ካልታከሙት የማይድን በሽታ ነው።» የሚለው ዐማራው ለኅልውናው የሚያደርገው ትግል ከገፋ፣ የማይነቀነቅ ፖለቲካዊ ኃይል ሆኖ ይወጣል፤ ይህ ደግሞ ግንቦት 7 ከቆመለት ዓላማ አንፃር ማለትም፣ ጠባቦችን፣ ተገንጣዮችን፣ ዐማራው ጠላታችን ነው ፣መጥፋት አለበት ብለው፣ በአርባ ጉጉ፣ በአሰቦት ገዳም፣ በምሥራቅና መምዕራብ ሐረርጌ ወዘተ የዘር ፍጅት የፈጸሙበትን ግለሰቦችና ቡድኖች በጥምረት ስም አሰባስቦ የፖለቲካው አውራ እሆናለሁ ብሎ ላሰላው ስሌት ከፍተኛ እንቅፋት ስለሚሆን፣ ዕውነቱን ነው፣ ከእሱ ዕይታ አንጻር አደገኛ ነው። ዐማራው ዛሬ እየሰበከ ያለው

ስለጎሳልውናው እንጂ፣ የኦነግ፣ የወያኔና የሸዕቢያ ዓይነት ብሔርተኝነትን አልሰበከም። ተሰብኮም ከሆነ፣ በአገር ወዳድነትና በብሔርተኝነት መካከል ያለውን የሰማይና የምድር የሚያክል ትልቅ ልዩነት አብራርቶ የማሳየት ኃላፊነት ያለው በኤፍሬም ዓይነቶቹ ላይ ነው።

«አገር ወዳዶች ሰዎችን ለያይተው የሚያዩበት መነጽር የላቸውም» ይላል ኤፍሬም። ይህን የማሳየት ኃላፊነቱ የማነው? በመጀመሪያ አገር ወዳዱ ማነው? አገር ጠዩስ? ይህን መለየት የግድ ይላል። በዚህ በኤፍሬም ዕይታ አገር ወዳዱ እሱ፣ አገር ጠዩ ለጎሳልውናው የሚጮኸው ዐማራውና የዐማራው ድርጅቶች መሆናቸው ነው። ያሳዝናል። «ደም ተቀብቶ ዝንብ አይፈሩም» ያልኩ ለዚህ ነው። ስንተዋወቅ! አገር ጠሉን ማን አንደ ሆነ ብትጠይቅ፣ ከኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አውራ ጠላት፤ ከዐማራው ደመኛ ጠላት ጋር የተሸጎጠ ነው እንደሚሉህ አትጠራጠር። ዓላማችችሁ ስንኩል ወንዝ ቀርቶ ሾለቁ የማይሻገር፣ ለማድረግ ቀርቶ ያላሰባችሁትን፣ ሌሎች የጣሩበትን የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የራሳችሁ አስመስላችሁና ሙሉ ዕምነት ጥላችሁ፣ በ 6 ወር አዲስ አበባ እንገባለን ብላችሁ ከሕዝብ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ሰብስባችሁ። ይኸው ዘጠኝ ዓመታት ተቆጠረ፤ እንኳን አዲስ አበባ ሊገባ ጂንካ መሠረት አልተጣለም! እንኳን በ 6 ወር አዲስ አበባ ለመግባት ይቅና፣ ጎንደር ላይ የፈነዳውን ሕዝባዊ አመጽ ለመደገፍ የሚያስችል የሰው ኃይል ቀርቶ፣ አንድ መሳሪያ እንኳ የማቀበል አቅም የሌላችሁ ባዶ መሆናችሁን ጊዜ አጋለጣችሁ።

«አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚመለከቱት እንደወገናቸው ነው።» ይለናል ኤፍሬም። ኤፍሬምና ድርጅቱ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን በዕኩልነት የሚመለከቱ ቢሆን፣ ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ፣ ዶ/ር አበባ ፈቃደ፣ አቶ ጌታቸው ረዳ፣ ወዘተ ለኢትዮጵያዊነትና ለዐማራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚናገሩ ሰዎች «የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ ነው» በሚባለው የግንቦት 7 ልሳን ኢሣት አንድ ቀን ድምፃቸውን እንሰማ ነበር። ይህም ኤፍሬምም ሆነ ድርጅቱ አንድም ኢትዮጵያዊ አይደሉል ፤ወይም የእነርሱ ኢትዮጵያነት መመዘኛ በደንባቸው እንደተገለጸው ከአማርኛ ውጭ ሌላ ቋንቋ የሚናገር ነው። ይህን ደግሞ ዶ/ር አሰፋ ነጋሽና አቶ ጌታቸው ረዳ ያሟሉ ነበር። አሰፋ ኦሮሚኛ አቀላጥፎ ይናገራል። ጌታቸው ትግርኛ አፍመፍቻ ቋንቋው ነው። ልዩነት አለ ከተባለ ሁለቱን በደቡብ ክልል የሚነገሩ አይደሉም የሚለው ይሆናል። እንግዲህ ኤፍሬም ኢትዮጵያዊ የሚለው ደቡብ ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ የተሟላ ኢትዮጵያዊነት አይደለም። ለኤፍሬም አንድ ጥያቄ ላቅርብ። ባንተ ዕይታ የኢትዮጵያዊነት የወል መገለጫ ዕሴቶች ምንድን ናቸው? ለዚህ ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ካለህ እርግጠኛ ነኝ የድርጅትክን ኤርትራ መመሽግ አውግዘህ፣ ምሽጉን ከኢትዮጵያውያን በተለይም ከዐማራው ልብ ውስጥ ታደርገዋለህ። ይህን መተመለከተ ፈቃደኝነቱ ካለህ እኔና አንተ በማናቸውም መድረክ በሕዝብ ፊት ክርክርና ውይይት እናድርግ?

7 «ዛሬ እያንዳንዳችን የፈለገውን ያህል ጠንካራ የብሔር ድርጅቶች ቢኖሩንም፣ ሕወሓትን በተናጠል ገጥመን ማሸነፍ አንችልም።»
ይህ አባባል ቀድሞ የመሸነፍና ጦር ሜዳ ሳይሄዱ ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ለጠላት እጅ መስጠት ነው። በመጀመሪያ ኤፍሬም ጠንካራ የብሔር ድርጅቶች መኖራቸውን ያምናል። ግን የትኞቹ እንደሆኑ አይጠቅስም። ከአጠቃላዩ መነሻ ሀሳቡ ስንነሳ የኢትዮጵያዊነት የሥጋት ምንጩ አድርጎ የሚጠቅሰው የዐማራውን የማንነት እንቅስቃሴ ነው። ይህ ደግሞ ብሔርተኝነትን የሚያቀነቅን አይደለም። ጎልውናን እንጂ!

በሌላ በኩል አገላለጹ «ቢኖሩም» የሚለው የቢሆን ቃል፣ ወደፊት ጠንካራ ብሔርተኛ ድርጅቶች ቢፈጠሩ እንኳን ወያኔን በተናጠል ገጥመን ማነሸነፍ አንችልም ሲል ይደመድማል። ይህም ግንቦት 7 ሲመሠረት ከሌሎች ውሻል ካለገኘ በቀር ብቻውን ታግሎ ወያኔን ለመጣል የማችይችል እንደሆነ አድርጎ እንደወሰነ ያሳያል። ለዚህም ይመስላል ከተለያዩ የብሔር ነፃ አውጭ ድጅቶች ጋር ኅብረት፣ ጥምረት፣ አንድነት፣ ውሕደት በሚሉ ማያያዣ ቃሎች አደረግን እያለ በተደጋጋሚ የሚነግረን።

ኤፍሬምና ድርጅቱ ወደ ትግል የገቡት በራሳቸው ማንነት፣ በማኅበረሰቡ ላይ በሚያሳድሩት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ጥንካሬአቸውንና አይበገሬነታቸውን አሳይተው ለድል እንደሚበቁ ራሳቸውን ያሳመኑ አይመስሉም። የድርጅትንም ትርጉም

በቅጡ የተረዱ አይመስሉም። ለዚህም ይመስላል ብርሃኑ ከዴምትና አርበኞች ጋር ጥምረት እንዲፈጠር የሻዕቢያ ሰዎች ሲያግባቡ፣ ዴምት በወታደራዊ አደረጃጀት፣ ግንቦት 7 ደግሞ በፕሮፓጋንዳ የተሻላችሁ ስለሆናችሁ ሁሉቱን በማጣመር ሥራ መሥራት ይቻላል ሲል፣ በብርሃኑ አንደበት የአውራምባ ታይምስ ያሰማን።

የፕሮፓጋንዳ ሥራ ውስብስብ መደራጀትን አይጠይቅም። አንድና ሁለት ሰዎች ሊሠሩት ይችላሉ። ቴክኖሎጂውም ለዚህ ያግዛል። የትጥቅ ትግሉ ግን ቀላል አይደለም። በመሆኑም ነው ግንቦት 7 «አድሮ -- » እየሆነ ያለው። «የተደራጁ ጥቂቶች ያልተደራጁ ሚሊዮኖችን ያሸንፋሉ» የሚለውን የሌኒንን ጥቅስ ያወቁ አይመስልም። ኤፍሬም ይህን ቢያውቅ ኖሮ፣ በተናጠል የፈለገውን ያህል የተጠናከረ የብሔር ድርጅት ቢኖርም፣ ወያኔን በተናጠል ማሸነፍ አንችልም ሲል አይደመድምም ነበር። ወያኔ ብቻውን ጠንክሮ ተደራጅቶ ነው የአንድነት ኃይሉን የበታተነው። የእኛ ቁርጠኝነት፣ ጽናት፣ ትዕግሥት፣ የጠላታችን ጥንካሬና ድክመት ለይቶ እና አበጥሮ የመለየት አቅም፣ የምንለውና የምንሠራው መጣጣም ካለ፣ ወያኔን አይደለም ሌላም ማሸነፍ ይቻላል። ለማሸነፍም የድጋፍ ሰጭውን ሕዝብ ስሜት እና እምነት ያገናዘበ፣ በወሬ ሳይሆን በተግባር የሚገለጽ ቁርጠኝነት ካለ፣ ወያኔን ለማንበርከክ የሚገድ ነገር አይኖርም። ውስጣችን ሲጠነክር፣ አቅማችን ሲጎለብት፣ እነአጅሮች የሚል ገናና ስም ከማጎበረሰቡ ሲቸረን፣ ከዚህም ከዚያም ድጋፉ ይጎርፋል። የእንተባበር፣ የአንድ እንሁን ጥያቄው በእኛ ልመና ሳይሆን፣ በሌሎች ጠያቂነት፣ በራሳችን ፍላጎት፣ ለዓላማችን ዳር መድረስ በሚያስችለን መንገድ የምናስተናግደው ይሆናል። ምንም ሳንሠራ፣ አንቱ፣ አጅሬ ሳንባል፣ በልመና የሚፈጠሩ ጥምረቶች ለድል አያበቁም። ውሽልሽሎች ናቸውና ! «በአህያ ቁርበት የተሠራ ቤት ይበጣጠሳል ጅብ የጮኸ ዕለት፣» የሚባለው ይሆናል። 8 «ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረኮች ላይ መሰማት የጀመረ አንድ እጅግ በጣም አደገኛ የሆነ ስብከት አለ። እሱም የ `` አማራው አማራ ሆኖ መደራጀት ፣የአማራንም የኢትዮጵያንም ነፃነት ያፋጥናል`` የሚለው ምንም ዓይነት መሠረት የሌለው ስብከት ነው።« ይለናል ኤፍሬም ማዴቦ።

ኤፍሬም ይህን ሲል ያለበትን ዘመን ያስተዋል አይመስልም። ይህ ዘመን የነዋለልኝ መኮንን፣ የነብርሃነ-መስቀል ረዳ፣ የነሥብሃት ነጋ፣ የነማርታ መብርሃቱ፣ የነዶ/ር ተስፋየ ደበሳይ፣ የነዘሩ ክሼን፣ የነፀጋዬ ገብረ-መድኅን፣ የነጌታቸው ማሩ፣ የነዶ/ር ሰናይ ልቁ፣ የነኃይሌ ፊዳ፣ ወዘተ ዘመን አይደለም። የዛሬው የዐማራ ወጣት፣የዐማራና የኢትዮጵያዊነት ጠላት የሆነው ሮማን ፕሮቻስካ በፃፈው የራስን በራስ ማጥፊያ ጽሑፍ አንብቦ በጭፍን የሚነጉድ አይደለም። እጅግ ዘግይቶ ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ዐማራን፣ ኢትዮጵያን፣ ኢትዮጵያዊነትንና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማጥፋት የተጀመረ እንደነበር ከታሪክ እና ከሁኔታዎች ተምሯል። የለውጡ ፍልጎት ከውስጥ በተፈጠረ ግፊት ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ከውጭ የተገፋና የተቀነባበረ እንደነበር ከተለያዩ መረጃዎች ከመገንዘቡም ሌላ፣ ኢትዮጵያና ዐማራው ከሚገኙበት ነባራዊ ሁኔታ ቁልጭና ፍንትው ብሎ በማሳየቱ የዐማራው ልጆች ነቅተዋል። ለካ! ብለዋል። እናም ካለፉት ትውልዶች ስሕተቶች ተምሮ፣ በወገኖቹ ላይ የተፈጸመውና እየተፈጸመ ያለው የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል አንገሽግሾት ዐማራ ነኝ ብሎ ተነስቷል። ይህን አቋም ሊቀለብሰው የሚችል ነገር የለም። ምክንያቱም ተፈጥሮአዊና የገዘፈ ዕውነት በመሆኑ። የዐማራው በዐማራነቱ መደራጀትም ዕውነት ነው። ግን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ፈጽሞ ሥጋ አይደለም። አይሆንምም። ዐማራው ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት «ሥጋት ይሆናል» ማለት፣«ብጥለው ገለበጠኝ» ዓይነት ነው የሚሆነው።

ዕውነታው ይሆኖ ሳለ፣ ኤፍሬም ማዴቦ የዐማራው በዐማራነቱ መደራጀት፣«እጅግ በጣም አደገኛ የሆነ ስብከት ነው» ካለ በኋላ መልሶ «ምንም ዓይነት መሠረት የሌለው ስብከት ነው»ይለናል። ስብከቱ መሠረት ከሌለው አደገኛነቱ ከምን ላይ ነው? በሌላ በኩል ዐማራው በቁጥሩ፣ በሥርጭቱ፣ በታሪኩ፣ በባህሉ፣ በኢትዮጵያዊነት ሥነልቦናው መደንደን፣ በአንድነትና በአብሮነት ስሜቱ የጠነከረ መሆን፣ ሁለመናዊ ኃይሉን አሰባስቦ ከብረት የጠነከረ አንድነቱን ዕውን ካደረገና ጎልውናውን በአስማማኝ ካረጋገጠ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መቀጠል አስተማማኝ መሠረት የሚሆን መሆኑ ዛሬ ብቻ ሳይሆን ፣ባለፉት ዘመኖች በታሪኩ ያረጋገጠው ዕውነት ነው። የኢትዮጵያ ጠላቶች በዐማራው ላይ የጥፋት ዘመቻ በወበራ የከፈቱትም ይህን ታሪኩን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው። እናም የዐማራው መደራጀትና ለኢትዮጵያ አንድነት መድኅን መሆን መሠረት የሌለው ሳይሆን፣ መሠረትም፣ ጣራም፣ ግድግዳም፣ ጭምጭምም ፣ማገርና ወራጅም ነው። ይህ ዕውነት ነው። ይህን መካድ ራስን መካድ ነው።

ለኤፍሬም ሥጋት የሆነበት ዐማራው እንደድሮው የሸዕቢያ፣ የወያኔ፣ የመኢሶን፣ የኢሕአፓ፣የወዝ ሊግ፣ የአብዮታዊ ሰደድ፣

ወዘተ ጉዳይ አስፈጻሚ ለመሆን ያልተዘጋጀ መሆኑ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የዛሬው ግንቦት 7 ተላካኪ፣ ብረት ነካሽ፣ ሰልፍ አድማቂ፣ የጊዜ፣ የጉልበት እና የገንዘብ አቅሙን አልገብርም ማለቱ ነው። ይህ ዕውነት ነው። ዐማራው ተዋርዶና ተንኳጦ፣ ተንቆና ተሰድቦ ሁሉንም በሆዱ አፍኖ በእሳና በይሉኝታ የሚኖርበት ጊዜ አክትሟል። «ለሁሉም ጊዜ አለው» የሚለው የጠቢቡ ሰሎሞን ምሳሌ ከዚህ ላይ ቦታው ነው።

የኢትዮጵያ አንድነት፣ ብሔራዊ ጥቅምና ሉዐላዊነት በአስተማማኝ ሁኔታ ሊረጋገጥ የሚችለው፣በባንዳዎችና በራስ ወዳዶች ሳይሆን፣ ኢትዮጵያዊነት ማንነቴ፣ እምነቴ፣ መመኪያዩ፤ ኩራቴና የእኔነት መገለጫዬ ብሎ በሚምነው፣ ኢትዮጵያዊነትን ከዐማራነት፣ ዐማራነትን ከኢትዮጵያዊነት ጋር ለንቅጦ የሁለት ድርብ ማንነቶች ባለቤት ነኝ በሚል ሕዝብ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ በዚህ ዕምነቱ ከውስጥ እስከ ውጭ፣ጠላቶቹ የበዙበት ዐማራው ነው። ዐማራውን ለአንድነትና ለኢትዮጵያዊነት ምስክር ቁጠር የሚለው ይኖራል ተብሎ አይገመትም። የቴዎድሮስ ፣ የምኒልክ፣ የዘውዲቱና የቀኃሥ ሥራዎች ለዚህ ነቃሾች ናቸው። ከዚህ ውጭ ለኢትዮጵያዊነትና ለአንድነት የሠራ አለ ካለ ማስረጃ የማቅረቡ ኃላፊነት የሚያርፈው በኤፍሬም ማዴቦ ላይ ነው።

9 «ዐማራው በዘር ተደራጅቶ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን በተለየ መንገድ የኢትዮጵያ ጠበቃ ይሆናል የሚለው አባባል፣ራስን አግዝፎ፣ወይም ሌሎችን አሳንሶ ከማየት የሚመነጭ የአዕምሮ በሽታ ነው፣» ይላል ኤፍሬም። ከዚህ ላይ ትንሽ መሥመር የዘለለና ወጥ የረገጠ አባባል ብሏል። ይህ አንድም ከታሪክ ዕውቀት ድህነት፣ ሁለትም ከፍፁም ክህደት የተሰነዘረ ሀሳብ ነው። ዐማራው እንኳን በዘመናዊ መንገድ ተደራጅቶ፣ በባህላዊ የገበሬ የክተት ሠራዊት የኢትዮጵያን አንድነትና ነፃነት በወሳኝነት ሲያስጠብቅ የኖረው ዐማራው ለመሆኑ ወዳጅ ቀርቶ ጠላት የመሰከረው ሐቅ ነው። የሩቁን ትተን የቅርቡን የአምባላጌን፣ የመቀሌን፣ የዐድዋን፣ የእንዳባጉናን፣ የሰለክላካ፣ የተንቤን፣ የማይጨውን፣ ከሁሉም በላይ የአምስት አመቱን የአርበኝነት ትግል እነማን ከአመራር እንከ ተዋጊ በብዛት ማን እንደነበር የአልቤርቶ ሳባቸን መጽሐፍ፣«ቀዩ አንበሳ» እና «የሀበሻ ጀብዱ» የተሰኙትን በውጭ ዜጎች የተጻፉትን ብታነብ ይህን ቀይ መስመር የዘለለ እና ወጥ የረገጠ ሀሳብ ልትጽፈው ቀርቶ አታስበውም ነበር። ዘመዶቻችን «ከመጠምጠም መማር ይቅደም» የሚሉት ከዚህ አይነቱ ስሕተት ለመዳን ነው።

ዐማራው በቁጥሩ፣ በታሪኩ፣ በሃይማኖቱ፣ በቋንቋው፣ በሥርጭቱ፣ በሥነልቦናው ግዙፍ ነው። ይህ የሚያጠያይቅ አይሆንም። አዎ! ዐማራው በሁለመናው የገዘፈ ነው። ነፍጠኛ ሲባል ዐማራው ይሸማቀቃል መስሏቸው፣ የበለጠ ነፍጠኛ እንዲሆን ገፋፉት እንጂ፣ አላሰፈሩትም። አንገቱንም አላስደፉትም። ኤፍሬም ራስን አግዝፎ ሲል፣ ዐማራው በይሉኝታ እንዳለፉት ሁሉ በሆዱ ይዞ ይቀመጣል መስሎት ይሆናል። ያ ዘመን አለፈ። ተነቃቃን። ሁሉም የሚመጥነውን፣ የአቅሙንና የድርሻውን እንጂ፣ አንዱ በሞተበት ሌላው የማዕዱን እንጀራ የአንበሳውን ድርሻ ልውሰድ የሚልበት ሁኔታ ምዕራፉ ተዘግቷል። እንደ አቅማችን ለማደር መዘጋጀት አለብን። ጥንቸል የጥንቸልን ያህል እንጂ፣ የአንበሳን ያልህ ላግሳ ብትል ትርፉ መፈንዳት ነው።

ዐማራው በእምነቱም፣በባህሉም በአብሮነት ስሜቱም ሌሎችን አሳንሶ ተመልክቶ አያውቅም። ቁጥር ግን ቁጥር ነው። ከኦሮሞው በስተቀር እስቲ የትኛው ነገድ ነው ከዐማራው ጋር በቁጥር እስተካከላለሁ የሚለው? ሌላውማ ሌላ ነው። ከየት መጥቶ! ስለሆነም የአዕምሮ በሽታ ያለበት «የገብርኤልን ግብር የበላ ለፍልፍ ለፍልፍ ይለዋል» የሚሉት ዓይነት የሆነው ነው ።

10 «የዐማራው በዘር መደራጀት የሚጠቅም ከሆነ፣የሚጠቅመው ይህን ዓላማ የሚያራምዱትን ጥቅት (ጥቂት ለማለት ይመስላል) የፖለቲካ ልሀቃን ብቻ ነው። ዕውነቱን እንነጋገር ከተባለ የዐማራው በዘር መደራጀት በአንድ በኩል ሕወሓት ከተቃዋሚው ጎራ የሚፈልገውን ትልቁ ሥጦታ ሲሆን፣በሌላ በኩል በኩል ደግሞ የዐማራው በዘር መደራጀት ኢትዮጵያ ከተጋረጡባት አደጋዎች ሁሉ ትልቁ ነው። ለዚህም ይመስለኛል የዐማራውን በዘር መደራጀት ከማንም በላይ አብዝቶ የሚኮንነው አማራው ሁሉ የሆነው» ይለናል ለኢትዮጵያ ብቸኛው አሳቢና ተቆርቋሪ ኤፍሬም ማዴቦ።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ አራት ታላላቅ ጉዳዮችን ኤፍሬም አንስቷል። የመጀመሪያው የዐማራው በዘር መደራጀት የሚጠቅመው የፖለቲካ ልሀቃኖቹን መሆኑን፣ ሁለተኛው የዐማራው በዘር መደራጀት ወያኔ ከተቃዋሚው ጎራ የሚጠብቀው ታላቅ ሥጦታ

አስገኝቶለታል፣ ሦስተኛው የዐማራው በዘር መደራጀት ኢትዮጵያ ከገጠሟት አደጋዎች ሁሉ ትልቁ ነው ፣ አራተኛ የዐማራውን በዘር መደራጀት ከማንም በላይ ዐማራው ይቃወመዋል የሚሉት ናቸው።

የዐማራው በዘር መደራጀት የሚጠቅመው ጥቂት የፖለቲካ ልሂቃንን ከሆነ፣ የኤፍሬም ማዴቦ ድርጅትም የተደራጀው ለደቡብ ሊሂቃን ጥቅም ነው ማለት ነው። በእርግጥ የአንድ ማኅበረሰብ ሊሂቃን የዚያ ማኅበረሰብ መብራቶች ናቸው። በሚሰጡት ብርሃንም እንደ ኅብረተሰቡ ዕድገት ደረጃ ተመጣጣኝ ጥቅም ማግኘታቸው ዕውነት ነው። ይህን ኤፍሬም ይስተዋል አልልም። ኤፍሬምን ያንቀጠቀጠው፣ የጥቂት ፖለቲከኞች መጠቀም ሳይሆን፣ ዐማራው በዐማራነቱ መደራጀቱና ለሌሎች አገልጋይነቱን አቁሞ፣ ለራሱ ኀልውና ከቆመ የግንቦት 7 ጥቅም ይቋረጣል ብሎ ከፍተኛ ሥጋት ያደረበት መሆኑ ነው። «የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል» እንዲሉ፣ የተለመደውን ገንዘብ ኤፍሬም በአውስትራሊያና በኒውዝላንድ ሳያገኝ በመመለሱ የፈጠረው «ባዶ እጄን ተመለስኩ» የሚለው ብስጭት የፈጠረበት መረበሽ ያስከተለው ክስ ነው።

ኤፍሬም ያላወቀው ትልቁ ነገር፣ ለገንዘብ ማጣቱ ዋናው ምክንያት ድርጅቱ ያስተላለፈው መልዕክት ነው። መልዕክቱም እንዲህ ነው። የግንቦት 7 አባል የሆነ ሁሉ፣ ዐማራው የሚያደርገውን የመደራጀት፣ የመሰባሰብና ዐማራ ዐማራ የማለት ጉዳይ እንዲያቆም፣ በተለይ ሞረሽ ወገኔ የተባለው ድርጅት የሚያደርገው የአውሮፓ፣ የአውስትራሊያና የኒውዝላንድ ጉዞ የተሳካ እንዳይሆን የምትችሉትን ሁሉ ሤራ ሥሩ ብሎ አዘዘ። ይህ ትዕዛዝ በቅንነት የሚያገለግሉትን የዐማራ ልጆች አስቆጣ። ይህም ለካ የሚባለው ዕውነት ነው ብለው፣ ድርጅቱን ከጥርጣሬ ባለፈ በተጨባጭ ግንቦት 7 ፀረ-ዐማራ መሆኑን በመረዳታቸው ኤፍሬም የፈለገውን ድጋፍ ሳያገኝ እንዲመለስ ግድ ብሎታል። ይህም ቁጭት ፈጥሮበት የዐማራውን በዘር መደራጀት የጥቂቶች መጠቀሚያ፣ ለወያኔ ጥቅምና ለኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ እንደሆነ የራሱን አደጋ ፈጣሪነት በዐማራው ለማመካኘት ሲሞክር ይታያል።

ሌላው የዐማራው መደራጀት ለወያኔ የሚጠቅም ከሆነ፣ ፕሮፌሰር አሥራትን አስሮ ባልገደላቸው ነበር። ቀጥሎም የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅትን ከፍተኛ በጀት በጅቶ ባላፈረሰ ነበር። የድርጅቱን አመራሮች ለዓመታት አስሮ ድርጅቱን ባልበታተነ ነበር። ወያኔን ከኤፍሬም በተሻለ አውቀዋለሁ። በግልጽ እንደሚታወቀው፣ ወያኔ ደደቢት ሲገባ ዐማራን አውራ ጠላቱ አድርጎ፣ ዐማራው ካልጠፋ የትግራይ ሕዝብ ማኅበራዊ ሰላም አያገኝም በማለት እርሱን ለማጥፋት ቆርጦ የዘመተ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም መሠረት ባለፉት 25 ዓመታት ከ 5 ሚሊዮን በላይ ዐማሮችን ከምድረ ኢትዮጵያ አጥፍቷል። ዐማራው የተፈጥሮ የመራባት መብቱን ከልክሎ ተተኪ ትውልድ አልባ አድርጎታል። በሙቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዐማሮችን የመኖር መብታቸውን ገፎ፣ ንብረታቸውን ዘርፎ ለችግር ዳርጓቸዋል። ይህም በመሆኑ፣ ወያኔ ከፍተኛ የሆነ የሥልጣን ተቀናቃኙ ዐማራው እንደሆነ ያውቃል። ለዚህም የመደራጀት ቀርቶ ሦስት ሆኖ የመቆምና የመቀመጥ መብት እንዲኖረው አይሻም። እናም የዐማራው መደራጀት ወያኔ የሚፈልገው ሳይሆን፣ አምሮ የሚጠላው፣ የሚፈራውና የሚያንቀጠቅጠው እንጂ፣ ይጠቅመኛል ብሎ የሚደሰትበት አይደለም። በተግባርም የምናየው ይህን ነው። የጎንደርና የጎጃም ሕዝባዊ አመጽ የወያኔን ኅልውና ከሚያሰጋ ደረጃ ላይ በማድረሱ፣ ወያኔ ሕገመንግሥቴ የሚለውን እና የሚመካበትን ሽሮ የአስቸኳይ ወታደራዊ አገዛዝ እንዲመሠርት ያስገደደው ዐማራው እንጂ፣ ግንቦት 7 አለመሆኑን ኤፍሬም ይስተዋል አይባልም። ይህም የዐማራው በማንነቱ መደራጀት፣ ለወያኔ ጥቅም ሳይሆን፣ ሞት መሆኑን እያየን ነው። ይህን ሐቅ ነው ኤፍሬም ማዴቦ ሊያስተባብል የሚጥረው። ገልብጦ ማንበብ ማለት ይኸ ይመስለኛል። ወይንም ዘመዶቻችን እንዲህ ያለነገር ሲገጥማቸው « ይቺ ወፍ ገልብጣ ነፋች» የሚሉት ዓይነት ነው።

ኢትዮጵያ እጅግ አደጋ የተጋረጠባት፣ የእኔ፣ እናቴ፣ ማንነቴ፣ ሃይማኖቴ ብሎ የሚያምናት የዐማራ ነገድ፣ በፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ-ዐማራ ቡድኖችና ኃይሎች የእርዳ ተራዳ ዘመናት ባስቆጠረ ትግል፣ ከራሱ አብራክ በወጡና ማንነታቸውን ክደው፣ በሌሎች አቻዎቻቸው የተካዱት ትውልዶች ድጋፍ ጭምር፣ ክንዶ ዝሎ፣ ኅብረቱ ላልቶ፣ ላለፉት 26 ዓመታት ኢትዮጵያ በጠላቶቿ እጅ መውደቋ ዕውነት ነው። የዐማራው ትውልድ ይህን ባለመገንዘብ ካራጆቹ ጋር መዋል፣ ኤፍሬም እንዳለው ለኢትዮጵያ አገራዊነት አደጋ ነው። ኤፍሬም ሻዕቢያ ዐማራንና ኢትዮጵያን ለማጥፋት ያደረገው የዘመናት ሤራና አሁንም እያደረገ ያለው ለኢትዮጵያ አደጋ መሆኑን አያምንም። አይቀበልም። ምሽጉ ነዋ! በዐማራው ትከሻ፣ ሕይዎት፣ ገንዘብና ሁለንተናዊ ዕርዳታ እጨብጣለሁ ብሎ ለቋመጠለት ሥልጣን እርካብ ይሆነኛል ብሎ ያሰላው ዐማራ፣ በማንነቱ ዙሪያ መሰባሰብ ሲጀምር፣ ኤፍሬምና ድርጅቱ ቆፈን ያዛቸው መሰል የዐማራ መደራጀት ለኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ ነው ይሉን ጀምር።

ልብ በሉ! ኤርትራውያን፣ ትግሬዎች፣ ኦሮሞዎች፣ ሲዳማዎች፣ አፋሮች፣ ጉራጌዎች፣ ከምባታዎች፣ ወላይታዎች፣ ሐረሪዎች፣ኦጋዴኖች፣ ወዘተ ወዘተ በነገዳቸው ዙሪያ ተደራጅተው የሚሹትን እያደረጉ ነው። አንዳንዶቹም ተገንጥሎ አገር ለመመሥረት ሕገመንግሥት አዘጋጅተዋል። እነዚህ ሁሉም ሲደራጁ ጠላታችን ነው ያሉት ዐማራውን ነው። በዚህም ከወያኔ ጋር አብረው አያሌ ዐማሮችን ገድለዋል፤ አሰቃይተዋል፤ለዚህ ማስረጃ« ምጽአተ ዐማራ» የተሰኘውን መጽሐፍ ልብ ያለው እንዲያነብና ዕውነቱን ከሐሰቱ እንዲለይ አደራ ለማለት እወዳለሁ።

ይህ ለኢትዮጵያ አደጋ መሆኑ ያልተከሰተለት ኤፍሬም፣ እንዴት ዐማራው ኅልውናየን ላስከብር ብሎ መሰባሰብ ሲጀምር፣ በምን ተዓምር የኢትዮጵያ አደጋ ይሆናል? ከሌሎች በተለየ ሁኔታ አደጋ የሚሆነው በምን ምክንያት ነው? ያውም ልገንጠል ሳይል? ነፃ አውጭ ሳያቋቁም? ኤፍሬምን ያሳሰበው ዐማራው እንደ ኢየሱስ በግ ማንም እየጎተተ ሊያርደው የማይችል፣ የማንም አፋሽ አጎንባሽ ከመሆን የራሱ ጌታና ባለቤት ለመሆን መወሰን፣ ለግንቦት 7 ግብር ከፋይ መጥፋቱ ነው።

በዚህ የኤፍሬም ባዶ ክስና ጩኸት ከዚያው በዚያው ራሱን በራሱ የሻረበት ሁኔታ ይታያል። ዐማራው በዘር መደራጀቱ ለኢትዮጵያ ከገጠሟት አደጋዎች ትልቁ መሆኑን ከገለጸ በኋላ፣ ለዚህም ይመስለኛል የዐማራውን በዘር መደራጀት ከማንም በላይ አብዝቶ የሚኮንነው አማራው ሁሉ የሆነው» ይለናል። ይህ ከሆነ ዐማራው አልተደራጀም ማለት ነው። የዐማራው መደራጀት በኢትዮጵያ ከገጠሟት ችግሮች ትልቁ ከሆነ፣ ባለመደራጀቱ ችግሩ የለም ማለት ነው። ዐማራው ለኢትዮጵያ ችግር ሆኖ እንደማያውቅ ሁሉ፣ ከእንግዲህም የኢትዮጵያ ችግሮች የመፍትሔ እንጂ፣ የችግሯ አካል አይሆንም። ማንነቱን ግን ያስጠብቃል። እርሱ ሲጠነክር ወዳጆቹ ይበዛሉ፤ ጠላቶቹ ይኮሰምናሉ። ኢትዮጵያ ከገጠሟት ሁሉ ከፍተኛው ችግር ግን ዋናውና ከፍተኛው፣ ከጠላቶቿ ጉያ ገብተው ፣ወዳጅ ጠላታቸውን በቅጡ ለይተው አምርረው እንዳይታገሉ እያደረጉት ያሉት ቡድኖች መበራከት ነው። ወያኔና ሻዕቢያ የተጣሉ መስሏቸው በሻዕቢያ እርዳት ወያኔን እንጥላለን በማለት ሕዝቡ ጠላትና ወዳጁን ለይቶ አምሮ እንዳይዋጋው የጭቃ እሾህ መሆናቸው ነው። የኢትዮጵያ አውራ ጠላት ወያኔ ሳይሆን ሻዕቢያ ነው። ወያኔ በሻዕቢያ ትከሻ ታዝሎ የመጣ ጎርፍ ነው። ወንዙ ከላይ ሲጠራ፣ ታች ያለው ተጠራርጎ ኩል የመሰለ ውኃ ይሆናል። በመሆኑም ወያኔና ሻዕቢያ በእርዳ ተራዳ የተመሠረቱ የኢትዮጵያና የዐማራው ጠላቶች ናቸው። ሻዕቢያና ወያኔ ያለመጣላታቸው ማሳያ የዴምትን ኃይል ተማምኖ ኤርትራ የገባው የግንቦት 7 አመራር፣ ምክት ሊቀመንበር አድርጎ የሾመው የዴምቱ ሞላ አስገዶም ዐርብ ተፈራርመው ሰኞ ጦሩን ይዞ አዲስ አበባ መግባት አንዱና ዋናው ነው። በኢትዮጵያ ያሉት ባለሥልጣኖች ሁሉም ከኤርትራ የሚወለዱ ናቸው። በጦርነቱ ከኢትዮጵያ ተባረው የነበሩ ኤርትራውያን እንዲመለሱ ሆነዋል። ንብረታቸውን ተረክበዋል። በአገሪቱ ዩኒቨርስቲዎች ከግማኛውም ነገድ በላይ የሚማሩት ኤርትራውያን ናቸው። ይህ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ እንዴት ተብሎ ወያኔና ሻዕቢያ ተጣሉ፣ በሻዕቢያ ድጋፍ ወያኔን እናስወግዳለን ይባላል? ለኢትዮጵያ አደጋው ይህ ዓይነት አስተሳሰብ ነው።

11 ኤፍሬም ማዴቦ እንዲህ ሲልም ይጠይቃል። « ለመሆኑ በዐማራው በዘር መደራጀት ኢትዮጵያ ተጎድታ አማራው የሚጠቀምበት ሁኔታ አለ? መልሱን ዐማራው በዘር መደራጀት አለበት ብለው ለተነሱ ጥቂቶች እተወዋለሁ» ይላል።

ላነሳው ጥያቄ መልሱን ሳይሰጥ «ጥቂቶች» ለሚለን መተው ከስሕተት ድኗል። ምክንያቱ እርሱ በእኛ እና በወገናች ላይ የደረሰው ቁስል ተሸካሚ ባለመሆኑ የሥቃዩን መጠን አያውቀውም። ለምን ራሳችን እንታደግ ብለን እንደተነሳን አይገባውም። እብን ነው። ሲጀመር ለዐማራው መደራጀት የሚጥሩ ኃይሎች ጥቂት ከሆኑ ጥያቄ የሚያስነሳ ነገር የለውምና ጥያቄው መነሳት አልነበረበትም። ምንዜም ኅብረተሰብ ነውና አብዛኛው ያልደገፈው፣ ያልተስማማበት፣ ያላመነበት ጉዳይ ወደ ተግባር አይለወጥምና የሥጋትም የድልም መሠረት አይሆንም። ኤፍሬም ዐማራው በዘር መደራጀቱ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ ነው ብሎ፣ እየተደራጀ ያለው ዐማራ ብዙ ሆኖ በተግባር እያየው፣ የእርሱም የድርጅቱም ኅልውና የቆመበት የዐማራ ግብር ከፋይ አሻፈረኝ ብሎ አውስትራሊያ ድረስ ተጉዞ የተለመደውን የግብር መጠን አጥቶ ተመልሶ፣ እንደራጅ የሚሉት «ጥቂቶች» ናቸው ማለት ራስን በራስ መቃረን ነው። አዎ! ምንጊዜም አዳዲስ ሀሳብ የሚያፈልቁ፣ የማኅበረሰቡን ችግር ቀድመው የሚረዱ፣ መፍትሔ የሚያመነጩ ጥቂቶች ናቸው። የዘመኑ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ፈጣሪዎች፣ የማኅበራዊ ለውጥ አስኳል የሆኑ የለውጥ ሀሳቦች አፍላቂዎች፣ ከጥቂቶች በታች የሆኑ የአንዳንድ ግለሰቦች የፈጠራ ውጤቶች ናቸው። ተጠቃሚው ግን የዓለም ሕዝብ በነቂስ ነው። በተመሳሳይ መንገድ የወያኔ የኢትዮጵያና የዐማራው ጠላት መሆንን፣ ከሻዕቢያ

የሚነሳ ኃይል ለዐማራውና ለኢትዮጵያ የሚፈይደው አንዳችም ነገር የለም ብለው ያሰቡ፣ ጥቂቶች መሆናቸው ዕውነት ነው። ሀሳባቸውን ግን ሁሉም ዐማራ ተቀብሎት እያራመደው ለመሆኑ ኤፍሬም ማዴቦ በዚህ ጽሑፉ ደጋግሞ ነግሮናል እና ፣የዐማራው መደራጀት ፍላጎት የጥቂቶች ሳይሆን፣ የምዕላተ ዐማራው ሕዝብ ሆኗል። ለዚህ የማኅበራዊ ሜዲያውን መከታተል ነው። የጎንደር ፣የጎጃም ፣የሸዋንና የወሎን ክፍለ-ሀገሮች እንቅስቃሴ መቃኘት ነው። የኤፍሬም ማዴቦ እና የድርጅቱ ልሳን የሆነው ኢሣት «የነፃነት ኃይሎች፣ የአማርኛ ተናጋሪዎች፣ የአርበኞች ግንቦት 7 » አርበኞች እያለ «ሀብት ያለው ያግባሽ ወይስ አፍ ያለው» እንደተባለው፣ መረጃው ተጣሞ ቢቀርብም፣ ዕውነታው የዐማራው የኅልውና ትግል መሆኑን ፣ዐማራው ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎችም ባይጥማቸውም እየመረራቸው የዋጡት ሐቅ ነው።

ኤፍሬም ማዴቦ ፣«በአማራው በዘር መደራጀት፣ ኢትዮጵያ ተጎድታ አማራው የሚጠቀምበት ሁኔታ አለ? ብሎ ጠይቋል። ለዚህ ጥያቄ ተገቢና የማያሻማ መልስ ለመስጠት በቅድሚያ ኤፍሬምና ግንቦት 7 ሊመልሱት የሚገባ ጥያቄ አለ። እርሱም በዐማራው መጥፋት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት ሁኔታ አለወይ? የዐማራው መጥፋት ለኢትዮጵያ እንደ አገር እና እንደ ሕዝብ መቀጠል ያስችላታል ወይ? የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ አዎንታዊ ከሆነ፣ ዐማራው፣ ዐማራ ጠፍቶ ኢትዮጵያ የምትባል አገር፣ ኢትዮጵያዊ የሚባል የዜግነት መታወቂያ ያለው ሕዝብም ይኖራል ብሎ አያምነም። ይህ እንዳይሆን ዐማራው ተደራጅቶ ኅልውናውን በማስጠበቅ የኢትዮጵያን አገራዊነትና አንድነት የማስጠበቅ ታሪካዊ ኃላፊነቱን ትናንት በእንትጮ፣ በድሆኖ፣ በጉራ፣ በጉንዳጉንዲት፣ በሣርውኃ፣ በመተማ፤ ከቱርኮች፣ ከግብፆችና ከድርቡሾች ጋር፣ በአምባላጌ፣ በመቀሌ፣ በዐድዋ፣ በእንዳባጉና፣ በሽሬ፣ በተንቤን፣ በማይጨው ከጣሊያን ጋር ባደረገው የሞት ሽረት ትግል ማንነቱንና ነፃነቱ አስጠብቆ ለዚህ ትውልድ እንዳሸጋገረ ሁሉ፣ ዛሬም ዐማራው በአባቶቹ ወኔና የአገርና የወገን ፍቅር ስሜት ተነሳስቶ፣ ማንነቱን በአስተማማኝ አስጠብቆ፣ የኢትዮጵያን አንድነት ያረጋግጣል። በመሆኑም ዐማራው በዐማራነቱ መደራጀት ለራሱም ለኢትዮጵያም ይጠቅማል።

ዛሬ ዐማራው እንደ ወደቀ ዛፍ ያገኘው ሁሉ በምሳር አናት አናቱን የሚለው፣ ዐማራ በመሆኑ ብቻ አይደለም። ዐማራ ሆኖ፣ ከሁሉም በላቀ ደረጃ ኢትዮጵያዊነኝ በማለቱ ነው። ጠላቶቹ ዐማራው ካልጠፋ ወይም በሁለመናው አናሳ ካልሆነ፣ ኢትዮጵያን እንደፈለግናት ማድረግ አንችልም ብለው ከልብ የሚያምኑ በመሆናቸው ከዘር ማጥፋት እስከ ዘር ማጽዳት የደረሰ ሠፊ ወንጀል እንዲፈጸምበት አድርገዋል። ይህን ድርጊት ያወገዘ ስንቱ ድርጅትና ቡድን እንደሆነ የምናውቅ እናውቃለን። ባጭሩ በዐማራው መደራጀት ኢትዮጵያዊነት ያብባል፣ አንድነት ይጠናከራል እንጂ፣ ኤፍሬም እንደሚለው የሥጋቻ ምንጭ አይሆንም። ሥጋቱ ያለውና የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ከልብ የሚያምነው ዐማራ አለመደራጀቱ ነው።

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት ዋስትና ነው!

ለምሥጋናም ሆነ ለወቀሳ፣ ለምክርም ሆነ ለተግሳጽ በሚከተለው ኢሜይል ይደርሰኛ